በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 243549
ጥቅምት 06 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ አብነት ገብረመስቀል ኦዳ - ጠ. አማረ አሸናፊ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሼክ መሀመድ ሁሴን አሊ አላሙዲ ጠ. ሚሊዮን አሰፋ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሥራ አሥኪያጅ እንዲሻር የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር ቅሬታ የቀረበው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 299862 በየካቲት 22 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በነሐሴ 20 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ቦሌ ታወርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በአመልካች እና በተጠሪ የተቋቋመ ሲሆን አመልካች 40% ተጠሪ 60% የአክስዮን ድርሻ አላቸው፡፡ ይህ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የንግድ ማህበር ከተቋቋመ ጀምሮ አመልካች ሥራ አሥኪያጅ በመሆን ሲሰሩ ቆይተዋል። 1ኛ. በማሕበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የማህበሩን የማይንቀሳቀስ ንብረት ስም ለማዛወር በቅድሚያ የማህበርተኞችን ስምምነት ማግኘት የሚያስፈልግ ሆኖ እያለ አመልካች የማህበርተኞችን ስምምነት ሳያገኙ እና ከተጠሪ የተሰጣቸውን የውክልና ስልጣን ተጠቅመው በቂርቆስ ክፍል ከተማ የሚገኙ 3383 እና 1971 ካ.ሜ ይዞታዎች ላይ ለቦሌ ታወርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የብር 120,000,000.00 የግንባታ ወጪ የወጣበትን በ2011 ዓ.ም እና በ2012 ዓ.ም ወደራሳቸው ስም አዛውረዋል። በዚህም በተጠሪ የአክስዮን ድርሻ ልክ ጉዳት አድርሰዋል። 2ኛ. አመልካች በማህበሩ ስም ከባንክ ብር 452,000,000.00 ተበድረው ለግል ጥቅማቸው አውለዋል። 3ኛ. ማህበሩ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ያሉትን የማህበሩን ሰነዶች ሁሉ አመልካች ለጠተሪ ወይም ለወኪላቸው እንዲያስረክቡ ሲጠየቁ ሰነዶቹ ለተጠሪ እንዳይደርሱ ከቢሮ በማውጣት ወስደዋል። እንዲሁም 4ኛ. አመልካች ስልጣናቸውን አላግባብ በመጠቀም የማህበሩ ስብሰባ እንዳይጠራ አድርገዋል።

በመሆኑም 1ኛ.አመልካች ከማህበሩ ሥራ አሥኪያጅነት እንዲሻሩ እና የማህበሩን ንብረት አዲስ ለሚሾም ሥራ አሥኪያጅ እንዲያስረክቡ፤

2ኛ. አመልካች ቦሌ ታወርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርን የሚመለከቱ የማህበሩን ዝርዝር የሂሳብ ሰነድ፣ የኦዲት ሪፖርት፣ የስብሰባ ቃለ ጉባኤ እና ሌሎች ሰነዶችን እንዲያስረክቡ እና

3ኛ. የማህበሩ ሂሳብ እንዲመረመር ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

አመልካች በሚያዝያ 18 ቀን 2014 ዓ.ም አሻሽለው ባቀረቡት መልስ ተጠሪ ከሥራ አሥኪያጅነት እንድነሳ የሚጠይቁት 120,000,000.00 ወጪ የወጣባቸውን ይዞታዎች ወደግላቸው አዛውረዋል እና 425,000,000.00 በማህበሩ ስም ተበድረው ለግል ጥቅማቸው አውለዋል በሚል ነው። በእነዚህ ምክንያቶች የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ከፍርድ ቤቱ የዳኝነት ስልጣን በላይ ስለሆነ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም። አመልካች የተጠሪ ወኪል ሆነው ሲሰሩ የነበረው በተጠሪ ሁሉም ድርጅቶች ላይ በመሆኑ አመልካች የውክልና ስልጣን በአግባቡ አልተወጡም በሚል ከሥራ አሥኪያጅነት እንድነሳ መጠየቁ ተገቢ አይደለም። በአመልካች በቦሌ ታወርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ላይ ጥቃቅን ግድፈቶች ተፈጽሟል ቢባል እንኳን አመልካች የተጠሪ ሌሎች ድርጅቶች በውክልና በማስተዳደሬ በተፈጠረ የስራ ጫና ምክንያት በመሆኑ አመልካችን ከሥራ አሥኪያጅነት ለማስነሳት በቂ ምክንያት አይሆንም። ተጠሪ በአመልካች ላይ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዘጠኝ መዝገቦች በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ደግሞ በአንድ መዝገብ በሰጠሁት ውክልና መሰረት ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ ጉዳት ደርሶብኛል በሚል ክስ አቅርበው እየታየ የሚገኝ በመሆኑ ከሥራ አሥኪያጅነት እንድነሳ በቀረበው ጥያቄ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሌሎቹን መዝገቦች ውጤት መጠበቅ ያስፈልጋል። የቦታ ስፋታቸው በክሱ የተጠቀሱት ይዞታዎች ከመነሻው የሊዝ ውል የተደረገው በአመልካች ስም እንጂ በቦሌ ታዎርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስም አይደለም። እነዚህ ይዞታዎች የማህበሩ እንዲሆኑ

የተስማማሁበት ውል የለም፡፡ በይዞታዎቹ ላይ የከተማ አስተዳደሩ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ተሰጥቶኛል፡፡ በእነዚህ ይዞታዎች ላይ ትክክለኛ ባለመብት ማን እንደሆነ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባለን ክርክር ውሳኔ ሳይሰጥ ከሥራ-አሥኪያጅነት ለማስነሳት የቀረበው ጥያቄ ተገቢነት የለውም፡፡ ምንም አይነት ሰነዶች ከቢሮ አላወጣሁም፡፡ አመልካች በተጠሪ 60% ድርሻ ላይ በውክልና ስልጣኔ እና በራሴ 40% ድርሻ ተገቢውን ውሳኔ በመወሰን አጠቃላይ የማህበሩን ስራ በማከናወን ማህበሩን ውጤታማ ያደረኩ በመሆኑ ስብሰባ እንዳይጠራ አድርጓል መባሌ ሀሰት ነው፡፡ ተጠሪ በወኪላቸው አመልካች አማካኝነት ሰነድ የማግኘት መብታቸውን ሲጠቀሙ ነበር፡፡ አመልካች ከሥራ አሥኪያጅነት የምነሳበት ምክንያት የለም እንጂ አለ ቢባል እንኳን ሌላ በሥራ አሥኪያጅነት ኃላፊነት የሚወስድ ሰው ማንእንደሆነ ሳይታወቅ ተጠሪ ሰነዶችን ለመረከብ ያቀረቡት ጥያቄ ተገቢነት የለውም፡፡ ድርጅቱ ዘመናዊ ህንጻወችን እየገነባ ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲውሉ ለማድረግ ማህበሩ የተመሰረተበት 545,000,000.00 ካፒታል ስለማይበቃ ከባንክ ብድር በመውሰድ እና በራሴ ገንዘብ የህንጻዎቹን ግንባታ ውጤታማ ሳደርግ ቆይቻለሁ፡፡ ከዚህ ማህበር ሥራ አሥኪያጅነት እንድነሳ ቢደረግ የህንጻዎቹ ግንባታ ጉዳት ላይ ስለሚወድቅ የማህበሩም ሆነ የሀገር ኢኮኖሚ ላይ ጉዳት ሊደርስ እንደሚችል ግምት ሊወሰድ ይገባል፡፡ ተጠሪ በተጨማሪ ማስረጃነት በማህበሩ ስም ከዳሸን ባንክ የተወሰደ ብር 425,000,000.00 በተለያየ ጊዜ ለአመልካች ቤተሰቦች መተላለፉን የሚያሳይ ቢሆንም ማስረጃው ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 137 መሰረት የቀረበ ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም፡፡ የብድር ውሉ እንዲፈርስ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ እልባት ሳያገኝ አመልካችን ከሥራ አሥኪያጅነት ለማስነሳት ክስ መቅረቡ ከቅን ልቦና ውጪ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር የንግድ ስራ ስሰራ ከመቆየቱ በተጨማሪ በግሉ የንግድ ስራ የምሰራ በመሆኑ የግሌንም ገንዘብ ወደማህበሩ ሂሳብ ሳስገባ ስለነበር ያወጣሁትም ገንዘብ የግሌ ነው ከሚባል በስተቀር በማህበሩ ስም የተወሰደ የብድር ገንዘብ አመልካች አውጥቷል የሚያስብል አይደለም፡፡ ፍርድ ቤቱ የሂሳብ ባለሙያ መድቦ እውነቱን ያጣራልኝ፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ክስ በበቂ ምክንያት እና በማስረጃ የተደገፈ ባለመሆኑ ውድቅ ይደረግልኝ ካልሆነም ሌሎች ክርክሮች እልባት እስኪያገኙ ይህ መዝገብ ለጊዜው ይዘጋልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ምስክሮች ሰምቶ አመልካች ከስልጣን አንጻር ላቀረቡት መቃወሚያ መሰረት ያደረገው የ120,000,000.00 እና የ425,000,000.00 የገንዘብ ክርክር ተነስቷል በሚል ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ የገንዘብ መጠኖች በተጠሪ የተጠቀሱት የአመልካችን ጥፋት ለማሳየት እንጂ ገንዘቡ ይመለስልኝ በሚል አይደለም፡፡ እንዲሁም አመልካች ከሥራ አሥኪያጅነት ሊነሱ ይገባል የሚለው የዳኝነት ጥያቄ በገንዘብ የማይተመን በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 18 እና በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 14 መሰረት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው፡፡ በተጨማሪም አመልካች ይህንን መቃወሚያ በቀድሞ መልሳቸው ላይ አቅርበው ውድቅ የተደረገ ሆኖ እያለ መልሳቸውን እንዲያሻሽሉ ሲፈቀድ በድጋሚ የሚያቀርቡበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ተጠሪ ክስ ያቀረቡት አመልካች የሥራ አሥኪያጅነት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ አልተወጡም

በሚል እንጂ በውክልና ስልጣና ጉዳት አድርሰውብኛል በሚል ባለመሆኑ አመልካች ከውክልና አንጻር ያቀረቡት መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም፡፡

የፍሬ ነገር ክርክሩን በተመለከተ አመልካች በምስክርነት ቀርበው ስብሰባ ለመጥራት እና ቃለጉባኤ ለመያዝ ጊዜ ያልነበራቸው በመሆኑ ሁሉም ነገር በቃል ይሰራ እንደነበር አረጋግጠዋል፡፡ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 8/1 ስር እያንዳንዱ የሂሳብ አመት ባለቀ በአራት ወር ውስጥ የማህበሩ ባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ መጠራት እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት ስብሰባ አለመጠራቱ እና ቃለጉባኤ አለመያዙ የአመልካችን ኃላፊነት ያለመወጣት የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች የተጠሪም ወኪል በመሆናቸው ማህበሩን በሙሉ ስለሚያስተዳድሩ ስብሰባ መጥራት አያስፈልጋቸውም ቢባል እንኳን ተጠሪ የሰጡት ውክልና ከተሻረ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ለሁለት የሂሳብ አመት ስብሰባ መጥራት እና ቃለጉ ባኤ መያዝ ነበረባቸው፡፡ ይህም አመልካች ማህበሩን በአግባቡ አለመምራታቸውን እና በንግድ ህጉ አንቀጽ 521/1 እና 522 መሰረት ጥፋት መፈጸማቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

እንደዚሁም አመልካች በሰጡት ምስክርነት የማህበሩን ሂሳብ መያዝ ከጀመሩ አምስት እና ስድስት አመት ብቻ እንደሚሆናቸው አረጋግጠዋል፡፡ ይህም ማህበሩ በተመሰረተ 20 ዓመት ውስጥ ለ15 ዓመት የሂሳብ ሰነድ ያልያዙ እና በንግድ ህጉ አንቀጽ 61 እና 425/2 በተደነገገው መሰረት ማህበሩን በአግባቡ ያልመሩ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች በፍርድ ቤቱ የማህበሩ ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ እንዲቀርብ በጠየቁት መሰረት በኤ.ኤ ብሮምሄድ ሰርቲፋይድ ኦዲት ፈርም በተባለ ድርጅት ተሰርቶ በቀረበ የኦዲት ሪፖርት የመነሻ ካፒታል መዋጮ በጥሬ ገንዘብ እንደተከፈለ ቢገለጽም በማህበሩ የባንክ ሂሳብ ገቢ መሆኑን ማረጋገጥ አለመቻሉን፤ መስከረም 25 ቀን 2011 ዓ.ም የማህበሩ ካፒታል ከ10,000,000.00 ወደ 600,000,000.00 ያደገ መሆኑ ቢገለጽም ያደገው ወደ 540,000,000.00 መሆኑን እና የካፒታል ጭማሪው በጥሬ ገንዘብ ይሁን በአይነት አለመታወቁን፤ የማህበሩ ካፒታል የሆነ 2000 ካ.ሜ ቦታ እስከአሁን ድረስ ስመሀብቱ ወደማህበሩ ሳይዞር በአመልካች ስም የሚገኝ መሆኑን፤ 1971 ካ.ሜ ይዞታ የማህበሩ ይሁን የአመልካች መለየት አለመቻሉን፤ የማህበሩን ሂሳብ ለመመርመር የተሟላ ሰነድ ባለመገኘቱ መመርመር አለመቻሉን፤ ለማህበሩ ህንጻ ግንባታ የወጡ ወጪዎች አለመመዝገባቸውን እና አመልካች 425,000,000.00 በማህበሩ ስም ከዳሸን ባንክ የተበደሩ መሆኑን ሶስት የብድር ውሎች የሚያሳዩ ቢሆንም ክፍያዎች በማህበሩ ሂሳብ ስላልተመዘገቡ የብድሩ ገንዘቡ ለማህበሩ ጥቅም ውሏል ወይም አልዋለም ማለት ያልተቻለ መሆኑን ገልጿል፡፡ አመልካች በዚህ የኦዲት ሪፖርት ላይ በሰጡት አስተያየት የኦዲት ሪፖርቱ በድጋሚ እንዲሰራ የጠየቁ ቢሆንም በሌሎች ማስረጃዎች አመልካችን ከሥራ አሥኪያጅነት የሚያስነሱ በቂ ምክንያቶች መኖታቸው የተረጋገጠ በመሆኑ የኦዲት ሪፖርቱን በድጋሚ ማሰራት አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ሰነዶችን በአግባቡ መያዝ የሥራ አሥኪያጅ ኃላፊነት ሆኖ እያለ ሰነዶች በአግባቡ ባለመያዛቸው ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ የአሰራር እና ከፍተኛ የአመራር ጉድለት መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች የሂሳብ ሚዛን፤ የኦዲት ሪፖርት፤ የስብሰባ ቃለጉባኤ እና ሌሎች ሰነዶችን ለተጠሪ ሰጥቻለሁ በሚል የሚከራከሩ ቢሆንም በማስረጃ አላረጋገጡም፡፡ እንደዚሁም የክርክሩ ሂደት በግራቀኙ መካከል በሌሎች 10 መዝገች ክርክር መኖሩን ያሳያል፡፡ አመልካች በሥራ አሥኪያጅነት እንዲቀጥሉ ቢደረግ የማህበሩን ጥቅም የሚያስጠብቅ ክርክር ያደርጋሉ ተብሎ አይገመትም፡፡ በአመልካች እና በማህበሩ ማካከል ይህ አለመግባባት እና የጥቅም ግጭት መኖሩ አመልካችን ከሥራ አሥኪያጅነት ለማስነሳት የሚያበቃ ምክንያት ነው፡፡ በተጨማሪም በ1971 ካ.ሜ እና 3383 ካ.ሜ በሆኑ ይዞታዎች የሊዝ ውል ማሻሻያ ሲደረግ የይዞታው ባለቤት አብነት ገ/መስቀል/ቦሌ ታወርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሚል መሆኑን የሊዝ ውሉ ያሳያል፡፡ ይዞታው የማነው? የሚለው በሌላ መዝገብ ውሳኔ የሚያገኝ ሆኖ አመልካች ይዞታው የራሳቸው ከሆነ በግልጽ በራሳቸው ስም ብቻ የማህበሩ ከሆነ ደግሞ በማህበሩ ስም ብቻ የሊዝ ውሉ ላይ እንዲጻፍ ማድረግ ነበረባቸው፡፡ አመልካች ይህንን ያለማድረጋቸው ማህበሩን በትጋት እና በጥንቃቄ ያለመምራታቸውን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ የማህበር ሥራ አሥኪያጅ የማህበሩ ወኪል እንደመሆኑ የማህበሩን ተልኮ ለማሳካት መስራት እንዳለበት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 515/2 ስር ተመልክቷል፡፡ አመልካች ከላይ የተዘረዘሩትን ጥፋቶች መፈጸማቸው በማህበሩ የተሰጣቸውን ውክልና በአግባቡ አለመወጣታቸውን የሚያሳዩ ስለሆነ 1ኛ. አመልካች ከሥራ አሥኪያጅነት ስልጣናቸው ተሽረዋል፤ 2ኛ. አመልካች ማህበሩን የሚመለከቱ የሂሳብ ሚዛን፤ የኦዲት ሪፖርት፤ የስብሰባ ቃለ ጉባኤዎች እና ሌሎች ሰነዶች ለተጠሪ ወይም ለወኪላቸው ያስረክቡ፤ 3ኛ. አመልካች የማህበሩን ንብረት እና ሰነዶች አዲስ ለሚሾመው ሥራ አሥኪያጅ ያስረክቡ፤ 4ኛ. የፍርድ በቤቱ ሬጅስትራር የሂሳብ ባለሙያ እንዲሾም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ቅሬታው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርሟል፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን የሰበር ቅሬታ አቅርበዋል፡፡

አመልካች በመጋቢት 01 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ ተጠሪ የብር 120,000,000.00 ክስ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡበት እለት ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነውን ክስ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ አመልካችን ከሥራ አሥኪያጅነት ለማስነሳት ያቀረቡት ክስ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክስ ጋር አንድ ላይ ማቅረብ ሲገባቸው ነጣጥለው ማቅረባቸው ተገቢ አለመሆኑን በመጥቀስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቤአለሁ፡፡ የስር ፍርድ ቤት አስቀድሞ በብይን ውድቅ የተደረገ ሆኖ እያለ በድጋሚ መልስ ሲሻሻል ውድቅ የተደረገ መቃወሚያ ሊቀርብ አይገባም በሚል ይህ መቃወሚያ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ በዚህ ምክንያት መቃወሚው መታለፉ በሰበር መዝገብ ቁጥር 160314 የተሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ የሚቃረን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት በፍርድ ሐተታው ላይ በግራቀኙ መካከል የይዞታ ክርክር መነሳቱ አመልካች የሥራ አሥኪያጅነት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ አለመወጣታቸውን ያሳያል የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ሥልጣን የለውም፡፡ ተጠሪ አመልካችን በዋነኛነት ከሥራ አሥኪያጅነት ለማስነሳት የጠየቁበት ምክንያት በተጠሪ የተሰጣቸውን ውክልና በአግባቡ አልተወጡም በሚል ነው፡፡ የውክልና

ጉዳይ ተቀላቅሎ መቅረቡ ተገቢ አለመሆኑን በመጥቀስ ክርክር ያቀረብኩ በመሆኑ በተሰጠኝ ውክልና መሰረት ኃላፊነቴን በአግባቡ መወጣት አለመወጣቴ በጭብጥነት ተይዞ ሊጣራ ይገባ ነበር፡፡ የስር ፍርድ ቤት ለውሳኔ መሰረት ያደረገው በተጠሪ ያልተነሱ ክርክሮችን ነው፡፡ የማህበሩን ሂሳብ ወቅቱን ጠብቆ አለመስራት፤ የሂሳብ ሚዛን እና የማህበሩን ሰነዶች በአግባቡ አለመያዝ የሚሉ ፍሬ ነገሮች በተጠሪ ክስ ውስጥ የተዘረዘሩ አይደሉም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ባልተጠየቀ ዳኝነት ውሳኔ መስጠቱ ዳኞች በሕግ መሰረት ብቻ መስራት አለባቸው የሚለውን የሕገ-መንግስቱን ድንጋጌ የሚቃረን ነው፡፡ በ2011 ዓ.ም የማህበሩ ካፒታል ሲያድግ የተያዘ ቃለ ጉባኤ በሰነዶች ማረጋገጫ ተመዝግቧል፡፡ ይህ ቃለ ጉባኤ በስር ፍርድ ቤት ቀርቦ እያለ አንድም ቃለ ጉባኤ አለመያዙ ተረጋግጧል ማለቱ ተገቢነት የለውም፡፡ የስር ፍርድ ቤት በሌሎች መዝገቦች ክርክር መኖሩ አመልካችን ከሥራ አሥኪያጅነት ለማስነሳት በቂ ነው ማለቱ ከስልጣኑ ውጪ ነው፡፡ በክርክሩ ላይ የተጠቀሱ ይዞታዎችም በአመልካች ስም የሚገኙ መሆኑን ለማሳየት ያቀረብኳቸው የሰነድ ማስረጃዎች በስር ፍርድ ቤት ሳይታዩ ታልፈዋል፡፡ በርካታ ግድፈቶች ያሉበትን የኦዲት ሪፖርት በመቃወም ያቀረብኩት አስተያየት ከፍርድ በፊት ብይን ሳይሰጥበት ከፍርድ ጋር ተጠቃሎ በድጋሚ የኦዲት ሪፖርት ሊሰራ አይገባም መባሉ ተገቢነት የለውም፡፡ የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው በአንድ በኩል ሰነድ የለም እያለ በሌላ በኩል ሰነድ አስረክብ ማለቱ ውሳኔው ሊፈጸም የማይችል መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከሥራ አሥኪያጅነት የሚያስነሳ በቂ ምክንያት ሳይኖር እንድነሳ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የአመልካች ቅሬታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች ከሥራ አሥኪያጅነት እንዲነሱ የተባለበትን ምክንያት ተገቢነት ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በሚያዝያ 16 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ አመልካች ከስራ አስኪያጅነት እንዲነሱ የተወሰነው ተፈጽመዋል የተባሉትን ጥፋቶች መፈጸማቸው በማስረጃ ተረጋግጦ ነው፡፡ እነዚህን ፍሬ ነገሮች እንደገና ማስረጃ በመስማት እና በመመርመር ለማጣራት ይህ ሰበር ችሎት ስልጣን የለውም፡፡ አመልካችን ከሥራ አሥኪያጅነት ለማስነሳት የተጠቀሱት ሁሉም ምክንያቶች መሟላት የግድ አይደለም፡፡ ሁሉም ምክንያቶች በቂ አይደሉም ቢባል እንኳን በንግድ ሕግ ቁጥር 514 መሰረት አመልካች ኪሳራ እንዲወሰንላቸው ከሚጠይቁ በስተቀር ወደ ሥራ አሥኪያጅነት ሊመለሱ አይችሉም፡፡ ከሥራ አሥኪያጅነት ለማስነሳት እና በሥራ አሥኪያጅ የደረሰውን ጉዳት በተመለከተ አንድ ላይ ክስ ሊቀርብ አይችልም፡፡ ለሁለቱ ክርክሮች የሚሰጠው መፍትሄ እና ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ድንጋጌዎች የተለያዩ ናቸው፡፡ የስር ፍርድ ቤት በጭብጥ አመሰራረት ረገድ የፈጸመው ስህተትም የለም፡፡ በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሕግ እና ማስረጃን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የአመልካች ቅሬታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በግንቦት 15 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታቸውን አጠናክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር፤ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው የተጠሪ የመጀመሪያው የዳኝነት ጥያቄ አመልካች ከቦሌ ታወርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሥራ አሥኪያጅነት እንዲነሱ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች ከሥራ አሥኪያጅነታቸው እንዲነሱ የዘረዘሯቸውን ምክንያቶች ተገቢነት ከመመርመራችን በፊት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሥራ አሥኪያጅ እንዲነሳ በፍርድ ቤት የሚወሰንበትን የህግ አግባብ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ የማህበር ሥራ አሥኪያጅ በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ወይም በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሊሾም እንደሚችል፤ ሥራ አሥኪያጁ በህግ፤ በመመስረቻ ጽሁፍ እና በመተዳደሪያ ደንብ ላይ የተሰጠውን ተግባር እና ኃላፊነት በተገቢው ጊዜ መወጣት፤ ጊዜውንም በሥራ ላይ ማዋል፤ ማህበሩንም በአግባቡ መምራት እና ማስተዳደር እንደሚጠበቅበት የንግድ ሕጉ 515 እና 516 ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡ እንደዚሁም በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ወይም በማህበርተኞች የተሾመ ሥራ ሰሥኪያጅ ከሥራ አሥኪያጅነቱ እንዲሻር ለፍርድ ቤት አቤቱታ ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ ሥራ አሥኪያጁን ከሥራ አሥኪያጅነቱ ሊያስነሳው የሚችል በቂ ምክንያት መኖሩን በማረጋገጥ እንዲሻር/እንዲነሳ ሊወስን የሚችል ስለመሆኑ በንግድ ህጉ አንቀጽ 517/3 ስር ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሥራ አሥኪያጅ እንዲሻር ከማህበርተኞቹ አንዱ ክስ ሊያቀርብ የሚችል ስለመሆኑ እና ፍርድ ቤቱም በቂ ምክንያት አለ ብሎ ሲያምን ከሥራ አሥኪያጅነት በመሻር የሚሰጠው ውሳኔ በህግ ተቀባይነት ያለው ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ሥራ አሥኪያጅን በፍርድ ቤት ለመሻር የሚያበቁ ምክንያቶች ምንድናቸው? የሚለው ነው፡፡ የንግድ ሕጉ ከሥራ አሥኪያጅነት ለመሻር በቂ የሚባሉት ምክንያች ምን እንደሆኑ በዝርዝር አያስቀምጥም፡፡ ከንግድ ሕጉ 517/3 አገላለጽ መገንዘብ የሚቻለው በቂ ምክንያቶች ምን እንደሆኑ የመወሰን ለፍርድ ቤቱ የተሰጠ ስልጣን መሆኑን ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም ይህንን ስልጣኑን ተፈጻሚ ሲያደርግ ወይም የቀረበውን ምክንያት በቂ መሆን ያለመሆን ሲመዝን ለሥራ አሥኪያጁ በማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ፤ መተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤዎች በሚወሰኑ ውሳኔዎች የተጣለበትን ሃላፊነት መወጣት አለመቻል፤ የማህበሩን የእለት ከእለት ተግባራት በቅርበት በኃላፊነት አለመምራት፤ ማህበሩ የተቋቋመበትን አላማ ከግብ ለማድረስ አለመቻል፤ የማህበሩን እና የማህበርተኞችን መብት እና ጥቅም የሚጎዱ ተግባራትን መፈጸም እና የመሳሰሉትን ምክንያች ከግምት ሊያስገባ ይገባል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በሥራ አሥኪያጅነት የተሾሙት በማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ሲሆን ተጠሪ አመልካችን ከሥራ አሥኪያጅነት እንዲነሱ በምክንያትነት የተጠቀሱት አራት ነገሮች ነው፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት በማሕበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የማህበሩን የማይንቀሳቀስ ንብረት ስም ለማዛወር በቅድሚያ የማህበርተኞችን ስምምነት ማግኘት የሚያስፈልግ ሆኖ እያለ

አመልካች የማህበርተኞችን ስምምነት ሳያገኙ እና ከተጠሪ የተሰጣቸውን የውክልና ስልጣን ተጠቅመው በቂርቆስ ክፍል ከተማ የሚገኙ 3383 እና 1971 ካ.ሜ ይዞታዎች ላይ ለቦሌ ታወርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የብር 120,000,000.00 የግንባታ ወጪ የወጣበትን በ2011 ዓ.ም እና በ2012 ዓ.ም ወደራሳቸው ስም በማዛወር በተጠሪ ድርሻ ልክ ጉዳት አድርሰዋል የሚል ነው፡፡ አመልካች በበኩላቸው ይህንን ምክንያት ለማየት ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለውም እንዲሁም ይዞታዎቹ የራሴ ናቸው የሚሉ መከራከሪያዎችን አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም በተጠሪ ክስ ከይዞታ አንጻር የተነሳው ክርክር አመልካችን ከሥራ አሥኪያጅነት ለመሻር የሚያበቃ ምክንያት መሆኑን ለማሳየት እንጂ ይዞታው ይመለስልኝ በሚል ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው በሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን ውድቅ ካደረገ በኋላ በእነዚህ ይዞታዎች ላይ የሊዝ ውል ማሻሻያ ሲደረግ የሊዝ ውል ተቀባይ አብነት ገብረመስቀል/ቦሌ ታወርስ ኃላፊነቱ የግል ማህበር ተብሎ መሞላቱ አመልካች የማህበሩን ስራ በትጋት እና በጥንቃቄ ሲመሩ እንዳልነበር ያሳያል የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎትም የስር ፍርድ ቤት ከይዞታ አንጻር የተነሳውን ክርክር ለማየት ስልጣን የለውም የሚል ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ በስር ፍርድ ቤት እንደተገለጸው ተጠሪ ከይዞታዎቹ አንጻር የጠየቁት ዳኝነት ይዞታዎቹ የማህበሩ ስለሆኑ ለማህበሩ ሊመለሱ ይገባል በሚል ሳይሆን አመልካች የማህበርተኞችን ፍቃድ ሳያገኙ የማህበሩን ይዞታ ወደራሳቸው ስም በማዛወር ጥፋት ስለፈጸሙ ከሥራ አሥኪያጅነት ሊሻሩ ይገባል በሚል ነው፡፡ ግራቀኙ ይዞታው የማነው በሚለው ላይ በሌላ መዝገብ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክር ያላቸው መሆኑን ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አመልካች የማህበሩን ይዞታ ወደራሳቸው ስም አዛውረዋል ወይስ አላዛወሩም የሚለው እና የይዞታው ባለቤት ማነው የሚለው በሌላ መዝገብ ላይ ባላቸው ክርክር እልባት የሚገኝ በመሆኑ እና በተያዘው መዝገብ ላይ በጭብጥነት ተይዞ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚችል ባለመሆኑ ከዚህ አንጻር የስር ፍርድ ቤቱ ይዞታው የማነው? እና ለማህበሩ ሊመለሱ ይገባል ወይስ አይገባም በሚሉት ነጥቦች ላይ የሰጠው ውሳኔ የለም፡፡ ይዞታው የማነው የሚለው በሌላ ክርክር እልባት የሚያገኝ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች የማህበሩ ሥራ አሥኪያጅ እንደመሆናቸው የማህበሩን ሰነዶች በአግባቡ ይዘዋል አልያዙም? የሚለው ከሥራ አሥኪያጅ ኃላፊነቶች አንዱ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ከይዞታዎቹ አንጻር የሰነድ አያያዝን መመርመሩ ከስልጣኑ ውጪ ጉዳዩን ተመልክቷል የሚያስብለው አይሆንም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አመልካች ይዞታዎቹ በእኔ ስም የሚገኙ ስለመሆናቸው የሚያሳዩ ሰነዶችን አቅርቤ ሳይታዩ ታልፈዋል በሚል ያቀረቡትን ቅሬታ ስንመለከት አመልካች በሊዝ ውል ማሻሻያዎች ላይ የይዞታዎቹ ባለቤት አብነት ገብረመስቀል/ቦሌ ታዎርስ ተብሎ መገለጹን ያልካዱ ሲሆን እኛም የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ውስጥ የሊዝ ውል ማሻዎች ላይ የአመልካች እና በማህበሩ ስም መገለጹን ተመልክተናል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች የይዞታው ባለቤት እኔ ስለመሆኔ ያሳዩልኛል የሚሏቸው ሰነዶች ሊመረመሩ የሚችሉት ይዞታው የማነው የሚለው ክርክር ሲመረመር እንጂ ከሥራ አሥኪያጅ መሻር ጋር ተያይዞ በተነሳ ክርክር ሊመረመሩ አይችሉም፡፡ በመሆኑም ለክርክሩ መሰረት በሆኑ ይዞታዎች ላይ የሊዝ ውል ማሻሻያ ሲደረግ ይዞታዎቹ የማህበሩ ከሆኑ በማህበሩ ስም ብቻ ወይም ይዞታዎቹ የአመልካች ከሆኑ

በአመልካች ስም ብቻ ሊገለጹ ሲገባ የሁለቱም ስም መጻፉ አመልካች የማህበሩን ሰነዶች በአግባቡ አለመያዛቸውን እና ስራቸውን በትጋት ሲወጡ እንዳልነበር ያሳያል መባሉ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ አመልካች ከሥራ አሥኪያጅነት እንዲሻሩ ያቀረቡት ሁለተኛው ምክንያት አመልካች በማህበሩ ስም ብር 452,000,000.00 ተበድረው ለግል ጥቅማቸው አውለዋል የሚል ነው፡፡ አመልካች በበኩላቸው በማህበሩ ስም ይህንን ገንዘብ መበደራቸውን ሳይክዱ ለግል ጥቅሜ አላዋልኩም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ይህንን ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው አውለዋል ወይስ አላዋሉም? የሚለው ግራቀኙ ባላቸው ሌላ ክርክር እልባት የሚያገኝ ሆኖ አሁንም ከሰነድ አያያዝ ጋር በተያያዘ አመልካች በማህበሩ ስም የተበደሩትን ገንዘብ ለማህበሩ ጥቅም ስለማዋላቸው የሚያስረዳ የወጪ ሰነድ ሊገኝ አለመቻሉን የስር ፍርድ ቤት በኦዲት ባለሙያ አረጋግጧል፡፡ ይህም አመልካች ከአንድ ሥራ አሥኪያጅ የሚጠበቀውን ሰነድ በአግባቡ የመያዝ ኃላፊነት አለመወጣታቸውን ያሳያል በሚል የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት የኦዲት ባለሙያውን ሪፖርት በመቃወም ያቀረብኩት አስተያየት ላይ ከውሳኔ በፊት ትእዛዝ ሳይሰጥ ከውሳኔ ጋር ተያይዞ ትእዛዝ መሰጠቱ ተገቢ አይደለም የሚል ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም ሊታይ የሚገባው እና ዋናው ነገር ፍርድ ቤቱ ለቀረበው መቃወሚያው እልባት መስጠቱ እንጂ መቼ እልባት ሰጠ የሚለው መሰረታዊ ለውጥ የሚያመጣ አይደለም፡፡

ሶስተኛው የተጠሪ ምክንያት አመልካች ስልጣናቸውን አላግባብ በመጠቀም የማህበሩ ስብሰባ እንዳይጠራ አድርገዋል የሚል ነው፡፡ ይህንን ፍሬ ነገር በተመለከተ ማስረጃ የመስማት እና የመመዘን ስልጣን ያለው የስር ፍርድ ቤት አመልካች ቢያንስ ከተጠሪ የተሰጣቸው ውክልና ከተነሳ በኋላ እንኳን ስብሰባ በመጥራት የያዙት ቃለ ጉባኤ አለመኖሩን አረጋግጧል፡፡ እንደዚሁም በተጠሪ የተጠቀሰው አራተኛው ምክንያት ማህበሩ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ያሉትን የማህበሩን ሰነዶች ሁሉ አመልካች ለተጠሪ ወይም ለወኪላቸው እንዲያስረክቡ ሲጠየቁ ሰነዶቹ ለተጠሪ እንዳይደርሱ ከቢሮ በመውጣት ወስደዋል የሚል ነው፡፡ ከዚህ አንጻርም የስር ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪ ሰነዶች እንዲያስረክቡ ሲጠየቁ ያስረከቡ ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ አለመኖሩን አረጋግጧል፡፡ አመልካች እንደክርክራቸው የሚያስረዱ ማስረጃዎችን እስካላቀረቡ ድረስ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ማድረጉ የሚነቀፍበት የህግ አግባብ የለም፡፡

በመሆኑም በስር ፍርድ ቤት አመልካች የማህበሩ ሥራ አሥኪያጅ በመሆናቸው በማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 7/ቀ የማህበሩን ሂሳብ መዛግብት እና ሰነዶች በዘመናዊ መልኩ የመያዝ እና በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 8/1 መሰረት የማህበሩን አባላት ስብሰባ የመጥራት እና ቃለ ጉባኤ የመያዝ ግዴታቸውን አልተወጡም በመባሉ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ ይህ ከሆነ ቀጥሎ መታየት ያለበት እነዚህ ምክንያቶች አመልካችን ከሥራ አሥኪያጅነት ለመሻር በቂ ናቸው አይደሉም የሚለው ይሆናል፡፡ ሥራ አሥኪያጅን ሊያሽሩ የሚችሉ ምክንያቶች በቂ መሆን ያለመሆናቸው ሲመዘን አንዱ ከግምት ሊገባ የሚገባው ጉዳይ ለሥራ አሥኪያጁ በማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ፤መተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በማህበሩ ጠቅላላ

ጉባኤዎች በሚወሰኑ ውሳኔዎች የተጣለበትን ሃላፊነት መወጣት አለመቻሉ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 8/1 እና በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 7/ቀ የተጣለባቸውን ሃላፊነት አለመወጣታቸው ከማህበር ሥራ አሥኪያጅነታቸው እንዲሻሩ ለማድረግ በቂ ምክንያቶች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ አመልካች ከቦሌ ታወርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሥራ አሥኪያጅነት እንዲነሱ ያቀረቧቸው ምክንያቶች በቂ ሆነው በመገኘታቸው የስር ፍርድ ቤት አመልካች ከማህበሩ ሥራ-አሥኪያጅነት እንዲሻሩ መወሰኑ እና በይግባኝ መጽናቱ የንግድ ሕጉን፣ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ እና የመመስረቻ ጽሁፍ የተከተለ ነው ከሚባል በስተቀር የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1ኛ. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 201893 በሕዳር 27 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 299862 በየካቲት 22 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ተብሏል፡፡

ትእዛዝ

1ኛ. በዚህ መዝገብ መጋቢት 07 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 03524 ላይ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

2ኛ. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 201893 በመጣበት አካኋን ተመላሽ ይደረግ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !